# "መኢአድን ለማጥፋት
# የረጅም ጊዜ ቅብብሎሽ"

የመኢአድ እውነተኛ የማዕ.ም.ቤት እና የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ለአቶ አበባው መሀሪ እውቅና ነፍገው በህገ-ወጥ መንገድ ላለመሠብሠብ በወሠኑት መሠረት ወያኔ ኢሕአዴግ፤ ምርሥጫ ቦርድና በአሥመሣዩ ሊቀመንበር በአቶ አበባው መሀሪ መካከል በተደረገው የረጅም ጊዜ ሥምምነት መሠረት ዛሬ የመኢአድ አባላትና አመራር ያልሆኑትን የገኸው ፓርቲ ሲብል የለበሱ የመከላከያ ሠራዊት እና የኢሕአዴግ ሊግ ወጣቶችን በሁለት መኪና ሙሉ በመኢአድ ጽ.ቤት ለሥብሠባ ቢያራግፋም ጠቅላላ ጉባኤውን ለማካሄድ በቁጥር ደረጃ ባለመሙላቱ ሌላ ተጨማሪ የጎዳና ተዳዳሪዎችን እድሚያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑትን በቀን 35 ብር እንደሚከፍሉ ቃል በመግባት ቢያሥገቡም ሊሣካ ባለመቻሉ ከቦርድ የተወከሉት ሠዎች ሦሥት ጊዜ ላለመታዘብ ከአዳራሹ ቢወጡም አቶ አበባው መሀሪ ለአለቆቻቸው በመደወል በአዳራሹ በተገኘው በጥቅማጥቅም በሠበሰቡት አድር ባይ ህዝብ ቁጥር 213 ኮረም ባልሞላ እንዲታዘቡ ቀጭን ትሥእዛዝ በመቀበል ከህግና ከመተዳደሪያ ደንብ ውጭ ሲታዘቡ ቆይተዋል።

በመኢአድ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የማዕ.ም.ቤት አባላት ብዛት እንደ ዞኖች ሥፋትና ጥበት ከ105 የላነሰ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ብዛት ከ600 ያላነሡ በመዋቅሩ መሠረት መሆን ሲገባው በ2005ኢ.ም ከተመረጡት የማዕ.ም.ቤት አባላት ውሥጥ ከ5የማይበልጡ ለጠቅላላ ጉባኤውም በድምሩ ከ12 የማይበልጡ በተገኙበት ከ200 በላይ የገኸውን ፓርቲ አባላትና ደጋፊ በመኢአድ ፅ.ቤት ውሥጥ አሥገብቶ ምርጫ ማካሄዳቸው መኢአድን በቅብብሎሽ ለማጥፋት የደረሱበትን ደረጃ ያመላክታል።

በዚሁ እንዲህ እንዳለ ድ.ቤት ውሥጥ በተሠበቡትና በእነ አበባው መከከል በተነሣ እምባጓሮ ከዚህ በፊት መኢአድን ለማፍረሥ ይንቀሣቀሱ ከነበሩት ውስጥ የህውሃት ተላላኪ በነበረው(መሀመድ ጋዳፊ) እና በብአዴን በኩል መኢአድን ለማጥፋት ይንቀሣቀሡ በነበሩ(የነ ማህተመ በኩረ ቡድን) በተነሣ ብጥብጥ የመሀመድ ጋዳፊ አይን በጩቤ በመወጋቱ ወደ ህክምና ተልኳል።

ይህ በእንዲህ እያለ ያለምንም ውይይት

1. ነባር አመራር ባልተገኙበት፤
2. የማዕ.ም.ቤት አባላት በደንቡ መሠረት ባልተሟሉበት፤
3. የኦዲትና ተመሣሣይ ሪፖርቶች ባልቀረቡበት በተለይ እነ አቶ አበባው ለግል ጥቅማቸው ያዎሉትን የ2007 ዓም የምርጫ ማሥፈፀሚያ 487,994.03 ብር ያልተዳሠሠበት፤
4. አሥመራጭ ኮምቴ ባልተመረጠበት፤
5.የመተደደሪያ ደንቡን አሸሽለናል ቢሉም ለአባላት በንባብ እንኳ ባልተሠማበት፤
6. የማዕ.ም.ቤት አባላት በአዲስ ባልተመረጠበት፤
7. የፕሬዚዳንት ምርጫ ጥቆማ ባልተካሄደበት በአቶ አበባው መሀሪ አቅራቢነት ድምፅ ሣይሠጥ ዶ.ር በዛብህ ደምሴ በሙሉ ድምፅ ተመርጧል መባሉ መኢአድን ለምልጥፋት መኢአድን መሥሎ የመገኘት ተልኳቸውን በምን ያህል ደረጃ ከፍ እንዳለ መገመት አያቅትም ለነገሩ በዚህ ወቅት የምርጫ ቦርድ ታዛቢዎች በፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ወቅት አልነበሩም ለአለቆቻቸው ምን እንደዘገቡ አብረን እንታዘባለን።

ከዚህ በፊት ጥቅምት 28-30/2007 ዓም በተካሄደው አሥቸኳይ የመኢአድ ሥብሠባ ወቅት እነ አቶ ማሙሸት በተመረጡበት ወቅት ህገወጥ ምርጫ ሥለሆነ አናፀድቅላችሁም በማለት ለቦርዱ ለሚታዘዙት ለእነአበባው መሀሪ ሰጥቻለሁ ምክንያቱም በደንባችሁ መሠረት የነማሙሸት አማረ እና የነማህተመ በኩረን ቡድን ሐምሌ 14 እና15 2005ዓም ባካሄዳችሁት 3ኛ መ&#0;/ጠቅላላ ጉባኤ ለዘለቄታው የአባረራችኋቸው ሥለሆነ ነው ባሉበት አፋቸው ዛሬ እነ ዶ.ር በዛብህ ደምሴ(የማህተመ በኩረ ቡድን) በ2005 የተባረሩትን እንዴት ይቻላል ወይሰ ያወጣችሁት መተደደሪያ ደንብ ለእኛ ሣይሆን ለእናንተ ነው የሚሠራው ይሉን ይሆን?

በጣም የሚገርመን ኢ.ር ሀይሉ ሻውል ፕ.ት በነበሩበት ወቅት በመተዳደሪያ ደንባችሁ መሠረት የፕሬዚዳንቱ የሥልጣን ጊዜ 2.ዓመት ሥለሆነ በደንባችሁ መሠረት ከልተዳደራችሁ ፓርቲውን እንዘጋዋለን እያሉ ማሥጠንቀቂያ በየሣምንቱ ይፅፉ የነበሩት ዛሬ በአቶ አበባው ጊዜ እሥከ ዛሬ (2 አመት ከ10 ወር ሙሉ)አለመፃፋቸው ሌላኛው አጋርነታቸውን ይገልፃል።

እዚህ ላይ ደሥ የሚለው "የበዮች አለመሥማማት ለተበይ ይበጃል" የሚለው የአባቶቻችን አባባል ቁልጭ ብሎ መታየቱ

ነው፡፡
ይኸውም አቶ አበባው መሀሪ ከመኢአድ መተዳደሪያ ደንብ ውጭ በመሄድ ፓርቲውን እያፈረሡ ነው በማለት
1.የሥልጣን የጊዜ ገደብ ሥለተገባደደ
2.በጥቅምት 29/2007አም በተካሄደው አሥቸኳይ የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ራሣቸውን ከሀላፊነት ማግለላቸው
3. ለምርጫ የተሠጣቸውን ገንዘብ ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው ... የፓርቲው ማዕከላዊ ኮምቴ ጥር 15 ቀን 2008 ዓም ባደረገው ሥብሠባ ከሀላፊነታቸው አግዶ ሀላፊነታቸውን ለህጋዊ አካል እንዲያሥረከቡ ውሣኔ ቢያሳርፍባቸውም ከምርጫ ቦርድ ጋር ተባብረው ለህጋዊ አካል ለማሥረከብ ፈቃደኛ ሥላልሆኑ ቦርዱንና አቶ አበባው መሀሪን ህጋዊ የፓርቲው ማዕ.ም.ቤት አባላት ከፍተኛው ፍ.ቤት ከሷቸው መጥሪያ ተቀብለው በ23/09/2008 ዓም መልሣቸውን በሬጅሥትራር በኩል አቅርበው የቃል ክርክሩ በ30/09/2008 ዓም እንዲካሄድ ትዕዛዝ ተሠጥቷል፡፡ ከላይ ያሉ ሥህተቶች ድምር እውነትን ለመፈፀም የአፈፃፀም ችግር የሌለበት የፍትህ አካላት ያለጥርጥር የበዮች አለመሥማማት ለተበይ ይበጃል የሚለው የአባቶቻችን አበባል ተግባራዊ ያደርጋል ብዬ አምናለሁ፡፡

"መኢአድ ከነሙሉ ክብሩ ህያው ነው"